የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 3
ADDIS ABABA, 2nd December, 2024


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፭፻፷፩/፪ሺ፲፯

የኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ……………......................................ገጽ ፲፯ሺ፫፻፸፬


**Content**


Regulation No. 561/2024

Council of Ministers Regulation Number 561/2024 of the Ethiopian Education and Training Qualifications Framework……………
………………................................Page 17374


**ደንብ ቁጥር ፭፻፷፩/፪ሺ፲፯**

**የኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሰረት የትምህርትና ስልጠናን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነት እና ጥራትን ማጐልበት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫዎች የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ፍላጐት መሠረት ያደረጉ እና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዜጐች በቀጣይነት ሊማሩበት፣ ሊሰለጥኑበት እና ሊያድጉበት የሚችሉበትን እድል ለማመቻቸት እና የህይወት ዘመን ትምህርትና ስልጠናን ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአፍሪካ ሀገራት በአህጉር ደረጃ ብሎም ቀጠናዊ የብቃት ማረጋገጫዎችን በማውጣት በጋራ ዕውቅና መስጠት እንዲችሉ ስምምነት በመኖሩና ኢትዮጵያም በአባልነት የፈረመች በመሆኑ ሀገራዊ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**REGULATION No. 561/2024**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON THE ETHIOPIAN QUALIFICATIONS FRAMEWORK FOR EDUCATION AND TRAINING**

**WHEREAS,** it is deemed necessary to enhance access, equity, relevance, and quality of education and training in accordance with the education and training policy;

**WHEREAS,** it is important to ensure that the qualifications provided are based on the universal needs of the Country and are of the required quality;

**WHEREAS,** it is crucial to provide opportunities for citizens to engage in continuous learning, training, and development, thereby fostering lifelong learning and training;

**WHEREAS,** there is an agreement that African Countries can jointly recognize each other by issuing Regional qualification certificates, and Ethiopia has ratified such agreements as a member state, it is necessary to develop a national qualification framework;

የሚኒስተሮች ምክር ቤት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ የሚኒስተሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፷፩/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ሀረጎች የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል፦

፩/ **“የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ”** ማለት ሀገራዊ መሰፈርቶችን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫዎች ምደባ፣ ልማት፣ዝግጅት፣ ንጽጽር እና ሽግግር ላይ የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ እውቅና ለመስጠት የሚያስችል መሳሪያ ነው፤

፪/ **“ሀገራዊ መስፈርቶች”** ማለት በአጠቃላይ ትምህርት፣ በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መስኮች ተፈላጊ የሆኑ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከትን ለመለካት የሚረዱ አስቀድመው የተወሰኑ ሀገራዊ መመዘኛዎች ናቸው፤

፫/ **“ንዑስ ማዕቀፍ”** ማለት በሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ስር የሚተዳደሩ የአጠቃላይ ትምህርት ንዑስ ማዕቀፍ፣ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ንዑስ ማዕቀፍ እና የከፍተኛ ትምህርት ንዑስ ማዕቀፍን የሚያካትት ነው፤

፬/ **“ብቃት”** ማለት አንድ ሰው በሥራ፣ በትምህርት፣ በሙያ እና በግል ዕድገቱ ስኬታማ ለመሆን የሚገለገልበት በተግባር የተረጋገጠ እውቀት እና ክህሎት ሆኖ ግላዊ፣ ማህበራዊ ስነ-ምግባራዊ እና የአመለካከት ወይም የስነ-ዘዴ ችሎታዎችን ያካትታል፤

**NOW, THEREFORE,** the Council of Ministers hereby issues this Regulation pursuant to Article 95 Sub-Article (1) of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the “Council of Ministers Regulation Number 561/2024 of the Ethiopian Education and Training Qualifications Framework”.

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, the words and phrases mentioned in this Regulation shall have the following meanings:

1/ “**Qualification Framework**” means a tool for recognizing the quality control of the classification, development, preparation, comparison, and transition of qualifications offered in Ethiopia based on national standards;

2/ **“National Requirements”** means predetermined national standards that help to measure knowledge, skills, and attitudes required in general education, higher education, and technical and vocational training;

3/ **“Sub-Framework”** means a sub-framework for general education, a sub-framework for technical and vocational training, and a sub-framework for higher education; the National Qualifications Framework manages all;

4/ **“Competence”** is a proven ability to use knowledge, skills, and personal, social, ethical, attitudinal, and methodological abilities, in work or study situations and professional and personal development;

፭/ **“ብቃት ማረጋገጫ”** ማለት አንድ ሰው በማዕቀፉ በግልፅ የተመለከቱትን የመማር ውጤት ወይም ብቃት መጨበጡን እውቅና በተሰጠው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ማስረጃ ነው፤

፮/ **“የብቃት ማረጋገጫ መግለጫ”** ማለት በብቃት ማዕቀፉ በተሰጡ እርከኖች ላይ የሚገኙ የብቃቶችን ዓላማና ባህርይ የሚገልጽ ማብራሪያ ነው፤

፯/ **“የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ”** ማለት አንድ ትምህርትና ስልጠናውን ያጠናቀቀ ሰው የሚኖረው ብቃትና የሚያከናውናቸው ተግባራት እንዲሁም በቀጣይ የሚወስዳቸው ትምህርትና ስልጠናዎችን የሚያካትት ነው፤

፰/ **“እርከን”** ማለት ከእውቀት፣ ከክህሎት እና ከብቃት እርከን ገላጮች አንጻር በማዕቀፉ ላይ በመደበኛነት የተሰየመ የብቃት መገኛ ደረጃ ነው፤

፱/ **“የእርከን መግለጫ”** ማለት በብቃት ማዕቀፉ ውስጥ በተወሰነ እርከን ላይ ተገቢውን ጥልቀት እና የመማር መጠንን የሚያመላክት ነው፤

፲/ **“የመማር ውጤት”** ማለት የመማርና የስልጠና ሂደትን ያጠናቀቀ ሰው ያውቃል፤ይረዳል፤ ወይም ይችላል ተብሎ የሚጠበቀው መገለጫ ነው፤

፲፩/ **“ጥራት ማረጋገጥ”** ማለት የትምህርትና ስልጠና ዝግጅት፣ ሂደትና ውጤት በተቀመጡ ወይም በታወቁ መስፈርቶች መሰረት መከናወኑንና በቀጣይነት መሻሻሉን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

፲፪/ **“ጥራት አረጋጋጭ አካል”** ማለት ጥራት እንዲያረጋግጥ ሥልጣን ባለው አካል እውቅና የተሰጠው ነው፤

5/ **“Certificate of Competence”** means a proof issued by an accredited body that a person has achieved the learning outcomes or competencies clearly stated in the framework;

6/ **“Qualification Statement”** is a description of the purpose and nature of the competencies within the levels given in the qualification framework;

7/ **“Qualification Level”** means the qualifications and activities that a person who has completed their education and training will possess, as well as the future education and training they may pursue;

8/ **“Level”** means a level of competence formally designated in the framework in terms of knowledge, skills, and competency level descriptors;

9/ **“Level Description”** means an indication of the appropriate depth and level of learning at a specific level within the competency framework;

10/ **“Learning Outcome”** means the profile expected of someone who has completed the learning and training process, including what they know, understand, and be able to do;

11/ **“Quality Assurance”** means the act of ensuring that the preparation, process and results of education and training are carried out according to established or known standards and are continuously improved;

12/ **“Quality Assurance Body”** means an accredited body that has the authority to ensure quality;

፲፫/ **“ሥልጣን የተሰጠው አካል”** አጠቃላይ የማዕቀፉን አተገባበር የሚቆጣጠር ተቋም ነው፤

፲፬/ **“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር”** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ሲሆን እንደአግባብነቱ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትርን ይጨምራል፤

፲፭/ **“አግባብነት”** ማለት በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ከግለሰባዊ ፍላጎት፣ ከማህበረ ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር እንዲሁም ከህይወት ዘመን ትምህርት ጋር የተጣጣመና ከአገራዊና ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎችና አውዶች ጋር የሚኖረው ተዛምዶ ወይም ግንኙነት ነው፤

፲፮/ **“ማዛመድ”** ማለት ተማሪዎች ወይም ሰልጣኞች ከአንድ የትምህርት ወይም የስልጠና ደረጃ ወደ ሌላ ለሚያደርጉት ሽግግር በብቃት ደረጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት እና ድንበር በግልፅ የሚወሰንበት እና መሸጋገሪያ የሚለይበት አሰራር ነው፤

፲፯/ **“ምዘና”** ማለት አንድ ተማሪ ወይም ተመዛኝ ከመማር ወይም ከሥልጠና የሚጠበቁ ውጤቶችን ወይም ብቃቶችን ስለመጨበጡ ለማረጋገጥ የሚደረግ የምዘና ሥልት ነው፤

፲፰/ **“ገምጋሚ”** ማለት በአንድ የተወሰነ የትምህርት ወይም ስልጠና መስክ የተሰማራ ሰው የተቀመጡ የትምህርትና ስልጠና ውጤቶችን ይዞ እንደሆነ የማረጋገጥ እና ውሳኔ የሚያሰጡት ብቃት ያለው የተመሰከረለት ፈታኝ ወይም መዛኝ ባለሙያ ነው፤

፲፱/ **“ክሬዲት”** ማለት በመማሪያ ጊዜ ወይም በተጨበጡ ብቃቶች መጠን ላይ ተመስርቶ ለትምህርት ውጤት እውቅና የሚሰጥበት መለኪያ ነው፤

13/ **“Authorized Body”** means the institution overseeing the framework’s overall implementation;

14/ **“Ministry or Minister”** means the Ministry of Education or the Minister, and where appropriate, it includes the Ministry of Labor and Skills or the Minister;

15/ **“Relevance”** means education and training provided in the field of education and training per individual needs, socio-economic interaction, and life-long learning, national and international trends and contexts;

16/ **“Articulation”** is a decision about the relationship between Two or more qualifications to establish clearly defined linkages that enable individuals to progress from One qualification to another;

17/ **“Assessment”** means a method used to ensure that a student or trainee has achieved the expected outcomes or competencies from learning or training;

18/ **“Evaluator or Assessor”** means an accredited person who makes assessment judgments about the learner's learning achievement to the specific learning outcomes;

19/ **“Credit”** means a measure of educational achievement based on learning time or the amount of competencies achieved;

፳/ **"ክሬዲት ማጠራቀም"** ማለት በትምህርቱ ጊዜ ወይም በስልጠናው ወቅት ለተገኙ የትምህርትና ስልጠና ውጤቶች ማሳያ የሚውል ተደማሪነትን የሚያሳይ ሂደት ነው፤

፳፩/ **"የህይወት ዘመን ትምህርት"** ማለት አንድ ሰው በህይወቱ ዘመን ሙሉ በቀጣይነት የሚማረው ዘርፈ ብዙና ሁሉን አካታች የሆነ ለግልም ሆነ ለማህበራዊ ልማት የሚውል የመማር ሂደት ነው፤

፳፪/ **"ቀድሞ ለተገኘ ትምህርትና ስልጠና እውቅና መስጠት"** ማለት አንድ ተማሪ ወይም ሰልጣኝ በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነ እና በኢ-መደበኛ መንገድ ያገኘውን እውቀትና ብቃት በምዘና በማረጋገጥ የሚሰጥ እውቅና ነው።

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ ደንብ በመንግሥት፣ በግል እና መንግሥታዊ ባልሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በሚሰጡ ሁሉም የብቃት ማረጋገጫዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ደንብ በሀይማኖት የትምህርት ተቋማት በሚሰጡ ሀይማኖታዊ ትምህርቶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፬/ <u>የማዕቀፉ መርህ</u>

ማዕቀፉ የሚከተሉት መርሆዎች ይኖሩታል፡-

፩/ አሳታፊነት

፪/ ፍትሀዊነት

፫/ ውጤት ተኮር

፬/ ተወዳዳሪነት

፭/ የህይወት ዘመን ትምህርትና ስልጠና

20/ **"Credit Accumulation"** means the process of adding credits to demonstrate the educational and training outcomes obtained during a course or training period;

21/ **"Lifelong Learning"** is a multi-dimensional concept of learning as a continuous, all-inclusive process of individual and societal development throughout life;

22/ **"Recognition of Prior Learning"** is formal recognition of a person's achievement of learning outcomes in formal, informal, and non-formal learning environments through a process of assessment.

## 3. <u>Scope of Application</u>

1/ This Regulation shall apply to all qualifications provided by public, private, and non-governmental educational and training institutions.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, this Regulation shall not apply to religious education provided by religious educational institutions.

## 4. <u>Principles of the Framework</u>

The framework shall be governed by the following principles:

1/ Participatory

2/ Fairness

3/ Result-Oriented

4/ Competitiveness

5/ Lifelong Education and Training

**፭. የማዕቀፉ ዓላማ**

ማዕቀፉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የብቃት ማረጋገጫዎችን የሚያስገኙ የትምህርት እና ሥልጠና ኘሮግራሞች ዝግጅት፣ አሰጣጥና ምዘና የሚመራባቸው ደረጃዎችና መስፈርቶች የማውጣት፤

፪/ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫዎች ከሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ የማድረግ፤

፫/ የብቃት ማረጋገጫውን የሚያገኙ ተመራቂዎች እና ተመዛኞች እንዲጨብጧቸው የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት፣ ክህሎት እና ብቃቶችን በተመለከተ ሀገራዊ ደረጃዎችን የማውጣት፤

፬/ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫዎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተዓማኒነት እንዲኖራቸው የማድረግ፤

፭/ በብቃት ማረጋገጫዎች መካከል ሽግግር የሚደረግበትን ስርዓት በመዘርጋት የብቃቶችን ንፅፅር ይበልጥ ግልጽነት የተላበሰ እንዲሆን የማድረግ፤ እና

፮/ ዜጎች በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነ እንዲሁም በኢ-መደበኛ ሁኔታ የህይወት ዘመን የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የማድረግ ናቸው፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ**

**፮. የማዕቀፉ እርከኖች እና የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች**

፩/ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፉ ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ስምንት እርከኖችና ሁለት የመዳረሻ እርከኖች አሉት።

፪/ ማዕቀፉ በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ አንድ፣ ሁለት እና ሶስት ላይ የተመለከቱ ስምንት እርከኖች፣ የብቃት ማረጋገጫዎች እና መግለጫዎች ይኖሩታል።

**5. Objectives of the Framework**

The framework shall have the following objectives:

1/ To establish standards and criteria for the preparation, delivery, and evaluation of education and training programs that lead to qualifications;

2/ To ensure that the qualifications offered align with the socio-economic needs of the Country;

3/ To establish national standards regarding the knowledge, skills, and competencies expected to be acquired by graduates and assesses who receive a qualification;

4/ To ensure that the qualifications provided have national and international credibility;

5/ To establish a system that facilitates the transfer between qualifications through a more transparent comparison of qualifications; and

6/ To ensure that citizens have access to lifelong education in formal, informal, and non-formal settings.

**PART TWO**

**QUALIFICATION FRAMEWORK**

**6. Levels and Types of Qualifications**

1/ The qualification framework has Eight levels, from level One to level Eight, and Two access levels.

2/ The framework consists of Eight levels, qualifications, and descriptors as indicated in tables one, Two, and Three of the appendix to this Regulation.

፯. ከፊል ብቃት ማረጋገጫ ስለመስጠት

፩/ በዚህ ደንብና ይህንን ደንብ መሰረት አድርገው በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት በመረጃ ቋት ውስጥ ተመዝግበው ከሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከፊል ብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይችላል።

፪/ አንድ ተማሪ ወይም ሰልጣኝ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ውስጥ የተመዘገበን ፕሮግራም ሙሉ ለሙሉ ሳይጨርስና የሚጠበቀው ብቃት ላይ ሳይደርስ የፕሮግራሙን የተወሰነ ክፍል፣ ኮርሶች ወይም ሞጁሎች ማጠናቀቁን ለማሳወቅ ከፊል የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጠው ይችላል።

፰. ከውጪ ሀገር ለተገኘ ትምህርትና ስልጠና ብቃት እውቅና መስጠት

እውቅና ካላቸው የውጪ ሀገር የትምህርት ተቋማት የተገኙ የብቃት ማረጋገጫዎች በኢትዮጵያ የብቃት ማዕቀፍ መመዘኛዎች መሰረት ተመዝነው እውቅና ይሠጣቸዋል።

፱. ቀድሞ ለተገኘ ትምህርትና ስልጠና እውቅና መስጠት

አንድ ሰው ቀደም ብሎ ለያዘው ብቃት በብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፉ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጠው ይችላል።

፲. የክሬዲት ማጠራቀም እና ማስተላለፍ

፩/ በተለያዩ የትምህርትና ስልጠናዎች በሚገኙ የብቃት ማረጋገጫ መካከል ተለዋዋጭ የሽግግር አማራጮችን በመፍጠር ለተማሪዎች ፍላጎት የሚሰማማ የትምህርት እና እድገት እድል በመፍጠር የክሬዲት ማጠራቀሚያ እና ማስተላለፊያ ስርዓት ይዘረጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ውስጥ የተመዘገቡ የብቃት ማረጋገጫዎችን ለማግኘት ወደ ሚያስችሉ ስልጠናዎች ለመግባት የሚከለክል ገደብ አይኖርም።

7. Provision of Partial Qualifications

1/ Educational and training institutions registered in the national database shall provide partial qualifications per this Regulation and the guidelines that form its basis.

2/ A student or trainee shall be awarded a partial qualification certification upon completion of portions, courses, or modules of a program without fully completing the program registered in the qualification framework.

8. Recognition of Foreign Qualifications

Qualifications from accredited foreign educational institutions will be evaluated and recognized according to the standards of the Ethiopian Qualifications Framework.

9. Recognition of Prior Learning and Training

A person may be granted a qualification, upon evaluation and assessment, under the qualification framework for their prior Learning and Training.

10. Accumulation and Transfer of Credits

1/ A flexible transition system will be established to facilitate the accumulation and transfer of credits, creating opportunities for education and growth tailored to the needs of students.

2/ There will be no restrictions on entry into training programs that lead to qualifications registered in the Ethiopian qualification framework, subject to the provisions of Sub-Article (1) of this Article.

**፲፩. <u>የማዕቀፍ መረጃ አስተዳደር ስርዓት</u>**

፩/ በኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ትግበራን የሚደግፍ አካታችነት ያለው ሀገራዊ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተደነገገው የመረጃ አስተዳደር ስርዓት የሚከተሉትን እውቅና የተሰጣቸው መዛግብትን ይይዛል፡-

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ፤
ለ) የስራ ቦታ ገምጋሚዎች፤
ሐ) የሙያ ማህበራት፤
መ) የግምገማ ማዕከላት እና የግምገማ መሳሪያዎች፤
ሠ) የምስክር ወረቀት ሰጪ አካላት፤
ረ) የትምህርት ስልጠና ተቋማት፤
ሸ) የጥራት ማረጋገጫ አካላት፤
ቀ) የጥራት ማረጋገጫ ደረጃ፤
በ) በውጭ ሀገር የተገኙ የብቃት ማረጋገጫዎች እና፤
ተ) የተማሪዎች ወይም ሰልጣኞች ውጤት።

**፲፪. <u>የብቃት ማረጋገጫ ስታንዳርድ</u>**

የብቃት ማረጋገጫ ስታንዳርድ የእያንዳንዱ ሙያ ምሩቃን ሊይዟቸው የሚገቡ የመማር ውጤቶች፣ አሰሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ፕሮፋል እና አስፈላጊ መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ ይዘጋጃል።

**፲፫. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ</u>**

፩/ በኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ የሚመዘገብ የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት ከትምህርትና ስልጠና በሚጠበቁ ውጤቶች፣ ምሩቃን ፕሮፋይል፣ የቅጥር እና የቀጣይ ትምህርት እድል መሸጋገሪያዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

**11. <u>Framework Information Management System</u>**

1/ An inclusive national information management system will be established to support the implementation of the qualification framework.

2/ The information management system will contain the following accredited records:

a) qualifications;
b) workplace evaluators and assessors;
c) professional Associations;
d) assessment Centers and Assessment Tools;
e) awarding bodies;
f) education and Training Institutions;
g) quality Assurance Bodies;
h) quality Assurance Standards;
i) foreign Qualifications;
j) academic records of students or trainees.

**12. <u>Qualification Standard</u>**

Qualification standards shall be designed to meet the learning outcomes that graduates of each profession should possess; the professional profile and requirements in accordance with the employers needs.

**13. <u>Qualification Registration</u>**

1/ Qualifications registered under the Ethiopian Qualifications Framework must consider the expected outcomes from education and training, the graduate profile, employment opportunities, and the potential for further education.

፪/ የብቃት ማረጋገጫዎችን እውቅና ለመስጠትና ለመጠበቅ መረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገቡ ይደረጋል።

2/ Qualifications shall be registered in a database for recognition and protection.

፫/ በመረጃ ቋት ውስጥ ለመመዝገብ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማሟላት ያስፈልጋል፦

ሀ) የብቃት ማረጋገጫውን የሚያስገኘው ፕሮግራም ርዕስ፤
ለ) የብቃት ማረጋገጫው ዓይነት፤
ሐ) የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል፤
መ) የትምህርትና ሥልጠናውን ለመስጠት እውቅና የተሰጠው ተቋም፤
ሠ) የብቃት ማረጋገጫ እርከን፤
ረ) የመግቢያ መስፈርት፤
ሰ) የተሰጠው ክሬዲት ዋጋ፤
ሸ) የብቃት ማረጋገጫ ምደባ፤
ቀ) የግምገማ እና ምዝገባ ቀናት፤
በ) የብቃት ማረጋገጫው ዓላማ፤
ተ) የመማር ውጤት መግለጫ፤
ቸ) ቀድሞ ለተገኘ ብቃት እውቅና ስለሚሰጥበት ሁኔታ፤
ኀ) የትምህርት ሥልጠናው ስለሚሰጥበት አግባብ፤
ነ) መስኩ በገበያ ላይ ስላለው ተፈላጊነት የሚገልጽ ማስረጃ፤
ኘ) ፕሮግራሙ ሲቀረጽ በመስኩ ያሉ ባለሙያዎች መሳተፋቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፤
አ) ፕሮግራሙ ሲቀረጽ ቀደም ብሎ ስምምነት በተደረሰባቸው የኢትዮጵያ መስፈርቶች እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ያካተታል።

3/ To be recorded in the database, qualifications must meet the following criteria:

a) title of the program;
b) type of qualification;
c) awarding body;
d) accredited Education and Training Institution;
e) level of Qualification;
f ) entry Criteria;
g) credit Value;
h) qualification Classification;
i) evaluation and Registration Dates;
j) the Purpose of the Qualification;
k) descriptions of Learning Outcomes;
l) recognition of Prior Learning Competency;
m) appropriation of educational training;
n) evidence for the demand of the field on the labor market;
o) evidence for the participation of industry experts in the formulation of a program;
p) evidence for the alignment of national and international standards of a program.

## ፲፬. <u>የብቃት ማረጋገጫዎችን ጥራት ማስጠበቅ</u>

፩/ በሀገር አቀፍ ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ ጥራት ማስጠበቂያ ሥርዓት ይዘረጋል።

## 14. <u>Assuring the Quality of Qualifications</u>

1/ A quality assurance system for qualification shall be established at the national level.

፪/ የሚዘረጋው ሥርዓት ሀገራዊ ሁኔታዎችና ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎችን ከግምት የሚያስገባ መሆን አለበት።

፲፭. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምዘና</u>

፩/ በኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማእቀፍ ስር ያሉ የትምህርትና ሥልጠና ውጤቶች የሚመዘኑበት መደበኛ መስፈርት ላይ ተመርኩዞ ይሆናል።

፪/ የምዘናውን ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የቅድመ ምዘና እና የድህረ ምዘና ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል።

፫/ የትምህርት ውጤት ከተግባር ፣ ከምዘና ዘዴዎች እና ከብቃት መስፈርቶች ጋር መናበብ አለበት።

፲፮. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

የትምህርትና ስልጠና መስኮችን የተከታተሉ ምሩቃን በዚህ ደንብ ከተደነገጉት እርከኖች ከሚጠበቀው እውቀት ክህሎት እና ብቃት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተዓማኒነቱ የተረጋገጠ የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የማዕቀፉ አስተዳደር</u>

፲፯. <u>የማዕቀፉ አስተዳደር</u>

፩/ የትምህርት ሚኒስቴር እና እንደአግባብነቱ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ይህን የብቃት ማረጋገጫ ማእቀፍ ለመተግበር የሚያስፈልጉ መመሪያዎችንና የአሰራር ማኑዋሎችን የማውጣት በበላይነት ያስተዳድራሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማዕቀፉን የማረጋገጥ ስራዎች እንደአግባብነቱ ለመንግሥታዊ ተቋማት እና ለሙያ ማህበራት እንዲሁም መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት በጊዜ ገደብ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

2/ The system to be developed should take national conditions and global trends into consideration.

**15. <u>Qualification Assessment</u>**

1/ Assessments shall be based on the standard criteria by which education and training outcomes are evaluated under the Ethiopian qualification framework.

2/ A pre-assessment and post-assessment system shall be implemented to ensure fairness.

3/ Education outcomes should be aligned along with practical assessment methods and qualification criteria.

**16. <u>Issuing Certificate of Qualification</u>**

1/ Graduates who attended the fields of education and training shall be given a certificate of competency verification that is equivalent to the expected knowledge, skills, and competence of the levels stipulated in this Regulation.

## <u>PART THREE</u>
## <u>MANAGEMENT OF THE FRAMEWORK</u>

**17. <u>Management of the Framework</u>**

1/ The Ministry of Education and, as appropriate, the Ministry of Labor and Skills shall oversee the promulgation of the guidelines and operational manuals required to implement this qualification framework.

2/ Subject to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the work of verifying the qualification framework may, as appropriate, be delegated to governmental institutions and professional associations, as well as non-governmental institutions by term limits.

**፲፰. <u>ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት</u>**

በሌሎች ህጎች የተሰጣቸው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በተቋማቱ የሚሰጡ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፉ ተፈላጊ ማስረጃዎችን የማደራጀት፣ ሲጠየቁ ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፣ የተቋምና የግለሰብ መረጃዎችን ደህንነቱን በጠበቀ መልኩ የመያዝ ኃላፊነት አለባቸው።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፱. <u>ቅድመ እውቅና ዕውቅና</u>**

፩/ በአሁኑ ወቅት በመሰጠት ላይ የሚገኙ የአጠቃላይ፣ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች ይህ ደንብ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ቅድመ እውቅና ተሰጥቷቸው በማዕቀፉ የመረጃ ቋት ውስጥ ይመዘገባሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ቅድመ እውቅና የተሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ቅድመ ዕውቅና ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ የሚፈለገውን መስፈርት ማሟላቱ ተረጋግጦ እውቅና ይሰጠዋል።

፫/ ደንቡ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ የሚከፈቱ አዳዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የተቀመጠውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ማሟላታቸው ተረጋግጦ ጊዜያዊ ምዝገባ ሳያስፈልጋቸው እውቅና ይሰጣቸዋል።

**18. <u>Institutions Providing Education and Training</u>**

Subject to their responsibilities under other laws, education and training programs provided by the institutions are responsible for organizing required evidence to pass through the eligibility system, passing it on to the relevant authority when requested, and keeping institutional and individual information securely.

## PART FOUR
## SPECIAL PROVISIONS

**19. <u>Pre-accreditation and Accreditation</u>**

1/ The general, technical and vocational, and higher education programs that are currently being offered shall be pre-accredited and registered in the framework's database within Two years from the effective date of this Regulation.

2/ Under Sub-section (1) of this Article, the pre-accredited education program is assured and recognized for meeting the required criteria within Two years from the date of prior accreditation.

3/ New education and training programs that will be opened after the approval of the Regulation shall be certified without the need for temporary registration if they fully meet the requirements.

**፳. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**20. Effective Date**

This Regulation shall be effective from the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 2nd Day of December,2024**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**